## የ BASF የቅሬታ ማቀበያ ዘዴ አሰራር ደንቦች

**የቀጥታ መስመሩን ማግኘት የሚችለው ማን ነው?**

የቀጥታ መስመሩ የ BASF ሰራተኞችን እንዲሁም ሶስተኛ ወገኖችን ጨምሮ፣ ሁሉም ሰው ሊያገኘው ይችላል።

**የትኞቹን ቅሬታዎች ማቅረብ ይችላሉ?**

የቀጥታ መስመሩ ጥያቄዎችን ሊጠይቁበት የሚችሉበት እና/ወይንም በትክክል የተፈጠረን ወይ ሊፈጠር የሚችልን በደል፣ የደንቦችን ወይንም የህጎችን እና የ BASFን ፖሊሲዎችን እንዲሁም የ BASF Global Code of Conduct (ዓለም ዓቀፍ የስነምግባር ደንቦች) ጥሰት ስጋትዎን ሪፖርት ሊያደርጉ የሚችሉበት ሚስጥራዊ ጣቢያ ነው።

ጥያቄዎች ወይንም ሪፖርቶች፣ እንደ የአካባቢያዊ እና ሰብዓዊ መብት ጉዳዮች፣ የመስሪያ ቤት ንብረት አያያዝ፣ የስልጣን ገደብ ደንቦች፣ ሙስና እና ጉቦ እንዲሁም የውሂብ እና መረጃ ጥበቃ ከመሳሰሉ ከማንኛውም የዓለም ዓቀፍ የስነምግባር ደንቦቻችን ምድብ ጋር ተያያዥ ሊሆኑ ይችላሉ።

**የቀጥታ መስመሩን እንዴት መድረስ ይችላሉ?**

የ BASFን Global Compliance Hotline (የዓለም ዓቀፍ ህግ ተገዢነት የቀጥታ መስመር) ወይ ከክፍያ ነፃ በሆነ ስልክ ቁጥር ወይንም ደግሞ በድረ-ገፁ በኩል ማግኘት ይችላሉ። ቀጥሎ ባለው ማስፈንጠሪያ እኛን እያገኙበት ያሉበትን ሃገር ስልክ ቁጥር ማግኘት ይችላሉ፦ EthicsPoint - BASF። የሚፈልጉም ከሆነ በድር-ቅፁ በኩል ሊያገኙን ይችላሉ፣ እባክዎን ይህን ማስፈንጠሪያ ይከተሉ፦ EthicsPoint - BASF። ምርጫዎ ከሆነ፣ እዚያ ውስጥ በተንቀሳቃሽ ስልክ የመድረሻ QR ኮድም ያገኛሉ።

**የእርስዎ ጥያቄ በእንዴት ይስተናገዳል የጊዜ ሰሌዳውስ ምንድን ነው?**

ወደ ስልክ ቁጥሩ በሚደውሉ ጊዜ፣ ጥሪዎ በጥሪ ማዕከሉ ተወካይ ይመለሳል። ምርጫዎ የሆነውን ቋንቋ ከመረጡ በኋላ፣ ራስ-ሰር የሆነ ማሳወቂያ በሂደቱ ውስጥ ይመራዎታል። ምርጫዎ የሆነው ቋንቋ የማይገኝ ከሆነ፣ ስጋትዎን ለመተርጎም የሚያግዝ ተርጓሚ ጥሪውን ይቀላቀላል። ጥሪዎች አይቀዱም፣ ምስጢራዊነት ሁልጊዜም ይጠበቃል። በተጨማሪም የቀጥታ መስመራችን በደንብ በተቋቋመ ውጫዊ የስልክ እና በድረ-ገፅ ላይ የተመሰረቱ የቀጥታ መስመር አገልግሎቶች አቅራቢ የሚመራ በመሆኑ፣ ይሄ የተረጋገጠ ነው።

ስጋትዎን በድር-ቅፁ ሪፖርት የሚያደርጉ ከሆነ፣ ቆየ ከተባለ በ48 ሰዓት ውስጥ ከ BASF የደርሶናል ማሳወቂያ ይደርስዎታል። የሪፖርትዎ ወይንም የጥያቄዎ ኤሌክትሮኒካዊ ማጠቃለያ፣ ግምገማ አድርገው ቀጣዩን እርምጃ ለሚወስኑ የተወሰኑ የ BASF ህግ ተገዢነት አባላት ብቻ የሚገኝ እንዲሆን ይደረጋል። እንደ ሪፖርቱ ዓይነት፣ ምርመራው ወደ ህግ ክፍል፣ የሰው ኃይል አስተዳደር፣ ኮርፖሬት ደህንነት፣ ኮርፖሬት ኦዲት ወይንም ወደ ኮርፖሬት EHS ሊመራ ይችላል።

ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ የቀጥታ መስመሩ በእርስዎ እና በምርመራ ቡድኑ ስም-አልባ ግንኙነት እንዲከናወን ማድረግ ይችላል። ስለዚህም፣ ሪፖርትዎን በመደበኛ መከታተል አስፈላጊ ነው። ለዚህም፣ ወደ ቀጥታ መስመሩ ደግመው መደወል፣ ወይንም ደግሞ፣ እኛን ለማግኘት የድር-ቅፁን ተጠቅመው ከነበር፣ የሪፖርት ቁልፍዎን እና ማለፊያ ቃል በመጠቀም ወደ ድረ-ገፁ መግባት ይችላሉ። የምርመራችን ውጤት እና የሚወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች ሚስጥራዊ ናቸው።

የምርመራ ቡድኖች ጉዳዮችን ለመገምገም እና መፍትሄ ለመስጠት በተቻላቸው መጠን በቅልጥፍና ይሰራሉ። እያንዳንዱ ምርመራ የተለያየ በመሆኑ ለጉዳዮች መፍትሄ ለመስጠት የሚወስደው የጊዜ ርዝመት ይለያያል። BASF ሁሉንም ጉዳዮች በፍጥነት ለማየት ጥረት ያደርጋል፣ ማለትም በወራት ፈንታ ሳምንታትን፣ ጉዳዩን በተመለከተ መልሶ እርስዎን ለማግኘት ደግሞ ቆየ ቢባል 3 ወራትን። ጉዳዩ ሲገባደድ፣ ማሳወቂያ ይደርስዎታል።

**ከበቀል እርምጃ እንዴት ይጠበቃሉ?**

BASF፣ በቅን ልቦና በመነሳሳት፣ ስጋቱን ሪፖርት የሚያደርግ ወይንም ምርመራ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ የሚደረግን የበቀል እርምጃ አይታገስም። ማንኛውም እንደዚህ ያለ የበቀል እርምጃ በ BASF ውስጥ በጥብቅ የተከለከለ ሲሆን እንደ ከባድ በደል የሚወሰድም ነው። ይሄ በተጨማሪም የእኛ Code of Conduct (የስነምግባር ደንብ) ላይ የተቀመጠ ነው። ስለዚህም፣ ስጋትዎችዎን በሚገልፁ ወይንም ምክር በሚሹ ጊዜ የበቀል እርምጃን መፍራት አያስፈልግዎትም።

እነዚህን ሪፖርቶች የሚቀበሉት የ BASF ሰራተኞች፣ የሚቀርቡትን መረጃዎች በከፍተኛ ሚስጥር እንዲይዙ የሰለጠኑ ናቸው። በተጨማሪም፣ የ “ማወቅ-ያስፈልገናል-መርህ” ነው የምንከተለው፣ ማለትም፣ መረጃውን መድረስ የተገደበ እና ጉዳዩን ለመከታተል መረጃውን በአስቸኳይ ለሚፈልጉ ብቻ የተፈቀደ ነው። በተጨማሪም፣ የገለልተኛነትን አሰራር ነው የምንተገብረው። ጉዳዮቹን የሚከታተሉ ሰዎች ገለልተኛ እንዲሁም ጉዳይ ክትትል እና የምስጢርነት ገደብ ላይም የማያዳሉ ናቸው።

**ስም-ዓልባ ሆነው መቆየት ይችላሉ?**

አዎ፣ ጉዳዮን ስምዎን ሳይጠቅሱ ማቅረብ ይችላሉ። ከዚያ በኋላ ጉዳዩን መከታተል ወይንም ተጨማሪ መረጃ ማካፈል ቢፈልጉ፣ አሁንም ስምዎን ሳይጠቅሱ በማንኛውም ሰዓት ሊያገኙን ይችላሉ።

በስም-ዓልባነትም ቢሆን ምናልባት BASF ጥያቄ ቢኖረው ወይንም ጥያቄዎን በተመለከተ ሊያገኝዎት ቢፈልግ መረጃ ይደርስዎት ዘንድ፣ የኢሜይል አድራሻዎን መስጠት ይችላሉ። BASFም ይሁን ውጫዊ የቀጥታ መስመር አቃራቢው የኢሜይል አድራሻዎን ማየት አይችሉም። ስለዚህም፣ ስም-ዓልባነትዎ የተጠበቀ ነው።

**የውጤታማነት ግምገማ**

የቅሬታዎች ማቀበያ ዘዴውን ውጤታማነት እንደ አስፈላጊነቱ፣ ግን ደግሞ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ እንገመግማለን።

**ብቃት**

በ BASF የሚገኘው የቀጥታ መስመር ውስጣዊ ብቃት፣ በኮርፖሬት ህግ ተገዢነት (compliance@basf.com) የሚገኝ ነው።